# ለክቡር ኢንጂነር ኀይሉ ሻውል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) መስራች እና ፕሬዘዳንት

አዲስ አበባ

ጉዳይ፤ የድጋፍ ደብዳቤ

ሰፕቴምበር አስራ ሁለት፤ ሁለት ሺህ ስምንት ዓ.ም

ክቡር ሆይ!

በኢትዮጵያ ዲሞክራስያዊ የመንግስት ስርአትን ለመምስረት የተጀመረው ረጅም ጉዞ በጎታች ህይሎች፤ በአንባገነኖች እና በጎሰኞች እየተጠለፈና እየተደናቀረ የሞት የሽረት ትግል ሲካሄድ እነሆ አያሌ ዘመናት አለፉ።

በዚህ ሂደት ለህገራችን ቅን የሚያስቡ ሀቀኞች የራሳቸውን ጥቅም ለህገራቸው አንድነት፤ ብልጽግናና እድገት ሲሉ ከማስቀረታቸውም በላይ ህይወታቸውን አሳለፉ። ግማሾቹም ስለቆሙለት አላማ ሲሉ “የሞት በቃ” ቢፈረድባቸውም በጽናት ቆመው እስከ መጨረሻ እስትንፋሳቸው ከአንዳሻው ገዢዎች ጋር የሚደረገውን ትንቅንቅ ቀጥለውበታል። እርሶ ከእነዚህ አይነት መረዎች አንዱ ሲሆኑ ለትግላችን መሳርያ ሆኖ እንዲረዳን ያቋቋሙት መኢአድ ደግሞ የትግሉ ግንባር ቀደም መሪ ፓርቲ ነው።

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ ከማንኛውም ፓርቲዎች ይልቅ ከፍተኛ ሚና የተጫወተው “መኢአድ” ከላይ እንደተጠቀሱት ሰዎች አይነት ሆኖ፤ ለኢትይጵያ አንድነት እና ለህዝቧ ድል ሲባል ተሰውቶ እንደነበር የሚታወቅ ነው። በዚህም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ያለማወላወል መልሱን ሰጥትዋል። ይሁን እንጂ በአንድነት ህይሎች መካከል ወያኔ/ኢሃድግ ያሰረጋቸው አፍራሾች በሰውም ሆነ በድርጅቱ በተከፈለው መስዋእትነት ላይ በመረማመድ ተልእኳቸውን አስፈጽመዋል። ለዚህ እኩይ ስራ የመጀመሪያው ጀብደኛ ልደቱ አያሌው ሲሆን እርሱም የፓርቲውን የኢዴፓን ፈቃድ መልሶ በቅንጅት ስም እንዲተካ የቀረበለትን ጥያቄ አሻፈረኝ በማለት ለወያኔ የነበርውን ታምኝነት አረጋግጧል። የእርሱንም የክህደት ስራ መሪነት በመከተል እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋም መሰሪና ጸረ የኢትዮጵያ ህዝብ አፍራሽ ስራቸውን በግልጽ አሳይተዋል።

የቅንጅትን ስም በባለቤትነት ለማስጠበቅ በእርሶ መሪነት በዙርያዎ በመሆን በህግ የተከላከሉት አባላት ሊደረግ የሚገባውን ሁሉ አድርገዋል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት ወያኔ የትግሉ ጽናት ከፓርቲው ስም እንጂ ከእነዚህ ጠንካራ አባላት ስላልመሰለው ያገለግሉኛል ለሚላቸው እና ህሊናቸውን ሸጠው ለሆዳቸው ላደሩት ለእነ አየለ ጫሚሶ የፓርቲያችንን ስም አሳልፎ ሰጥትዋል። አርማውንም ለአገልጋዩ ለልደቱ አያሌው ለግሶታል። በዚህ ሂደት ወያኔ ያልገባው ነገር ቢኖር ቅንጅት ማለት ኀይሉ ሻውል ማለት መሆኑን ነው። ቅንጅት ማለት ጌታቸው መንግስቴ፤ አባይነህ ብርሀኑ እና ሌሎች ከማእከላዊ ኮሚቴ እስከ የገጠር እና የከተማ ወረዳ አባላት ብሎም እስከ ዲያስፖራው ሌት ተቀን ካለማቋረጥ የሚንቀሳቀሱ አባላት መሆናቸውን ነው። በአጠቃላይም ወያኔ ያልተረዳው ቅንጅት ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ነው።

ዳሩ ግን በእርሶ የሚመራው ማእከላዊ ኮሚቴ ሁሉን ነገር በትእግስት ካስተዋለ በኋላ ለቅንጅት ሰፊ መሰረት የጣለውን እና የኢትዮጵያን ህዝብ ጥያቄ ለመመለስ ተሰውቶ የነበረውን መኢአድን እንደገና



EthioLion.Com

ወደ ትንሳዔ ብርሃኑ እንዲያንሰራራ በማድረግ ትግሉ ከቆመበት እንዲቀጥል የተወሰደው እርምጃ የጠላትን መንደር እንዲሸበር አድርጓል። ይህ የተሸበረው የጠላት ሀይል ዝም ብሎ አልተቀመጠም። አሁንም እስር እስራችን የሚሉትን ወኪሎቹን “ጃስ” ብሎ በአንድነታችን ላይ ሊያስጨህ ሞክሯል። በተለይም በዲያስፖራው ይህ ጎልቶ የታየ ቢሆንም “በመኢአድ” ፓርቲያችን ደጋፊዎች ብርታት የተከፈተው አፍ ተጠርቅሟል። ስለዚህም ከእንግዲህ ወደፊት እናጂ ወደ ኋላ የለም።

ክቡር ፕሬዘዳንት፤

በአያሌ ታጋዮች ደም የተገነባውን “መኢአድን” እንደገና የፓርቲያችን መጠሪያ ስም እንዲሆን የተላለፈውን ከፍተኛ የፖሊሲ ውሳኔ እኛ በአሜሪካ የምንገኝ ስማችን ከዚህ በታች የተጠቀሰው ቻፕተሮች ከልብ እንደግፋለን። ይህንንም ድጋፋችንን የመኢአድ ማእከላዊ ኮሚት አባላት እንዲያውቁት እንዲያደርጉልን በማክበር እንጠይቃለን። በዚህ አጋጣሚ ለማንኛውም ግዳጅ ከጎኖ እና ከፓርቲያችን ጎን እንደምንቆም እያረጋገጥን በግሎ ትግሉ እንዲያጎመራ የሚያድርጉትን ጥረት የምናደንቅ መሆናችንን እንስታውቃለን።

መኢአድ የኢትዮጵያ መሪ ፓርቲ ነው!

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆችዋ ከወደቀችበት ተነስታ እንደገና ታብባለች!

1. አትላንታ
2. ቦስተን
3. ዳላስ
4. ፍረዝኖ
5. ላስቬገስ
6. ሎስአንጀለስ
7. መንፊስ
8. ሜሪላንድ
9. ናሽቪል
10. ኒውዮርክ
11. ኦክላንድ
12. ሳንዲያጎ
13. ሲያትል
14. ሳንፍራንሲስኮ
15. ሳክራሜንቶ
16. ቨርጂኒያ

መኢአድን በሙሉ ድምጽ እንደግፋለን!

መኢአድ አሜሪካ!

Ethiopia Will Prevail!

EthioLion.Com